# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

አንብበው ያስነብቡ! አባዝተው ያሰራጩ!

የግንቦት 7 ድምጽ፤ ቁጥር 327 ነሃሴ 9 2006 ገጽ 1

ግንቦት 7: የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ ወያኔን ለማስወገድ የተሻለ ነው ብሎ ያመነበት የትግል ስልት - ሁለገብ የትግል ስልት ነው። በዚህ የትግል ስልት መሠረት ሕዝባዊ ተቃውሞ፣ ሕዝባዊ እምቢተኝነት እና ሕዝባዊ አመጽ ተደጋግፈውና ተናበው መሄድ አለባቸው ብሎ ያምናል። ስለሆነም እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ በአመቸውና በሚያምንበት መንገድ ለትግሉ አስተዋጽኦ የማበርከት እድል አለው።

ከግንቦት 7 ዕርሰ-አንቀጽ የተወሰደ (ገጽ-2)

## በተለያዩ አሜሪካ ግዛቶች የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን አገረቸዉን ከወያኔ መዐት ለማዳን መቁረጣቸዉን ተናገሩ

በአሜሪካ የተለያዩ ግዛቶች የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን አገራችንንከውድቀት መታደግ የወቅቱ አንኳር ጥያቄ ነው በማለት ከሦስት ሺህዓመታት በላይ በህልውናዋ ፀንታ የቆየችውን ይህችን አገር የዛሬዎቹ ፋሽስቶች ሲሸራርፏትና ለባዕዳን አሳልፈው ሲሸጧት እጃችንን አጣምረን ዳር ቆመን ልንመለከት አይገባም በማለት የትግል ጥሪ ማቅረባቸውን ዘጋቢዎቻችን ያደረሱን መረጃ ያመለክታል። ሟቹ መለስ ዜናዊ ስልጣን እንደጨበጠ የባንዲራችንን ታሪካዊነትና ኢትዮጵያዊ ቅርስነት በማንቋሸሽ ከተራ የዱቄት መቋጠሪያ ጨርቅ እንደማይለይ አድርጎ መናገሩን ያስታወሱት አስተያየት ሰጭዎቹ አገራችን እንደ አገር በልበ ሙሉነት እንዳትቀጥል ገና ከማለዳው የወጠኑት ስልት መሆኑን መረዳት አያዳግትም ሲሉ ተናግረዋል። የፋሽስቱ ወያኔ ጸረ-ኢትዮጵያዊነትከሁዋላ ታሪኩ ጋር ተያይዞ የመጣ መሆኑንም አመልክተዋል።

ኢትዮጵያውያኑ አክለውም አምባገነናዊ ባህሪው ከዓመት ዓመትእየጨመረ የመጣው ፋሽስቱ ወያኔ፤ በዘር ከፋፍሎ የኢትዮጵያንአንድነት ለማዳከም የቀየሰው ስትራቴጂና የወጠነው ሴራ ( ወደ ገጽ 2 ዞሯል )

## ቴዎድሮስ አድሃኖ "የድምፃችን ይሰማን" መሪዎችን ከጓንታናሞ እስረኞች ጋር ማገናኘቱ ብዙዎችን አስቆጣ

የሙስሊሙን ማህበረሰብ የመብት ጥያቄ በማስተባበር ላይ የሚገኘው ድምፃችን ይሰማ የጉጅሌው ወያኔ ተላላኪ ቴዎድሮስ አድሃኑ በእስር ላይ የሚገኙትን የሙስሊም መፍትሄ አፈላላጊ ኮሚቴአባላትን አስመልክቶ ለአንድ መቀመጫውን አሜሪካ ላደረገ የፋሽስቱ ወያኔ ደጋፊ ሬዲዮ የሰጠውን መግለጫ አስመልክቶ ማብራሪያ እንዲሰጥ ጠይቋል።

የፋሽስቱ ተላላኪ ቴዎድሮስ አድሃኖ በእስር ላይ ያሉ የመፍትሄ አፈላላጊ ኮሚቴ አባላትን ጓንታናሞ ከታሰሩ አሸባሪዎች ጋራ ግንኙነት እንዳላቸው አረጋግጠናል ሲል የተለመድ የቅጥፈት ውንጀላውን በንፁሃኑ ህዝበ ሙስሊም ላይ ሰንዝሯል። የወያኔው ቱልቱላ ቴዎድሮስ የሰነዘረው ውንጀላ በበርካታ ህዝብ ዘንድመነጋገሪያ መሆኑ የታወቀ ሲሆን ውንጀላውን ተከትሎ በጉዳዩ ዙሪያ በርካታ አስተያየት ሰጭዎች ሃሳባቸውን በመሰንዘር ላይ ሲሆኑ ውንጀላው ሆን ተብሎ ፋሽስቱ ወያኔ በሙስሊሙ ማህበረሰብ ዘንድ እየደረሰበት የሚገኘውን ተቃውሞ በማስፈራራት ለማስቆም የተሸረበ ( ወደ ገጽ 4 ዞሯል )

## የመከላከያ ሰራዊት አባላት ወያኔን ዘረኛ ስርዐቱን እየከዱ በመጥፋት ላይ ናቸዉ

በሁሉም የመከላከያ እዞች ከዕለት ዕለት እጅግ ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው የሰራዊት አባላት በመክዳት ከነ ሙሉ ትጥቃቸው በመጥፋት ላይ መሆናቸውን የውስጥ ምንጮቻችን አመለከቱ። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ እረፍት ተቀብለው ቤተሰብ ለመጠየቅ በሚል የሚሄዱ የሰራዊቱ አባላትም ሙሉ በሙሉ ለማለት በሚያስደፍር መልኩ ወደ ግንባር እንደማይመለሱና በፋሽስቱ አገዛዝ ሊደርስባቸው ከሚችለው አደጋ ራሳቸውን ለማዳን ከአገር እንደሚሰወሩም ለማወቅ ተችሏል። ቤተሰብ ለመጎብኘት በሚል እረፍት የወጡ የሰራዊት አባላትን እንዲያፈላልጉ የተላኩ የጦር አመራሮች ጭምር ከሄዱበት እንዳልተመለሱ የደረሰን መረጃ ያመለክታል። የውስጥ ምንጮቻችን እንዳመለከቱት የሰራዊቱን መክዳት ተከትሎ የፋሽስቱ ወያኔ ጦር በሰው ሃይል ረገድ እየተመናመነ መምጣቱንና ይህም የአገዛዙን ቱባ የጦር መሪዎች እንቅልፍ እንደነሳቸው ተመልክቷል።

የአገዛዙ ዘረኝነት፤ አምባገነናዊነት፤ በሰራዊቱ አባላት በተደጋጋሚ የሚቀርበው የጥቅማ ጥቅም ጥያቄ በአገዛዙ ተቀባይነትባለማግኘቱ በሰራዊቱ ውስጥ ከፍተኛ ቅራኔን በመፍጠሩ አሁንም ድረስ በሁሉም ( ወደ ገጽ 2 ዞሯል )

## ወያኔ በግንቦት 7 ንቅናቄ ዙሪያ የተለመደ የቅጥፈት ድራማ እየሰራ መሆኑ ታወቀ

በተለያዩ ጊዜያት በውሸት የታጨቁ የማወናበጃ ዶክመንታሪ ድራማዎችን በመስራትና በመልቀቅ የህዝብን ስነ ልቦናና ትግል ለማድከም የሚሰራው ፋሽስቱ ወያኔ አሁንም በነፃነት አርበኛው አቶ አንዳርጋቸው ፅጌና እሳቸው በሚመሩት የግንቦት 7 ንቅናቄ ዙሪያ አዲስ የፈጠራ ድራማውን ለማዘጋጀትና ለመልቀቅ ላይ ታች እየማሰነ እንደሚገኝ የውስጥ ምንጮች አመለከቱ። በፋሽስቱ ወያኔ እጅግ አረመኔያዊ የአካልና የስነልቦና ስቃይ እየተፈፀመባቸው በጨለማ እስር ቤት ተወርውረው የሚገኙትን የግንቦት 7 ዋና ፀሃፊ አቶ አንዳርጋቸው ጽጌን ክብር ለመንካትና ለማዋረድ ብሎም የኢትዮጵያ ህዝቡ በግንቦት 7 ላይ የሰነቀውን የነፃነት ራዕይ ጥላሸት ለመቀባት በማሰብ በግንቦት 7 የፍትህ፤ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ ላይ ተስፋ አታድርጉ አይነት መልዕክት ለማስተላለፍ ታስቦ ድራማው እንደተቀናበረም ለማወቅ ተችሏል።

የዘረኛው ወያኔ አገዛዝ በሚያቀነባበረው የፈጠራ ድራማ ላይ ተሳታፊ የሚሆኑ ግለሰቦችን ከፍተኛ ገንዘብ ፈሰስ በማድረግ በማሰልጠን ላይ መሆኑም ታውቋል። በፈጠራ ድራማው ላይ የተለያዩ በአገር ቤት የፖለቲካ እንቅስቃሴ ውስጥ ንቁ ተሳታፊ የነበሩና አሁን በእስር ላይ የሚገኙ ግለሰቦችን ለመንጀውል በሚያስችል መልኩም እንደተቀናበረ ለማወቅ ተችሏል። በተጨማሪም በፈጠራ ድራማው ላይ በኢትዮጵያውያን ድጋፍ እየተጓዘ አራት አመታትን ያስቆጠረውን የኢትዮጵያ ሳተላይት ቴሌቭዥን ኢሳት የግንቦት 7 ልሳን ነው ብሎ ( ወደ ገጽ 4 ዞሯል )

## አሜሪካ ዴንቨር "እኔም አንዳርጋቸው ጽጌ ነኝ" በሚል አርዕስት ዙሪያ የተሳካ ስብሰባ ተካሄደ

ቅዳሜ ኦገስት 9, 2014 ቀን በአሜሪካ ኮሎራዶ ዴንቨር ግዛት በተካሄደው ታላቅ ህዝባዊ ስብሰባ የግንቦት 7 ንቅናቄ የህዝብግንኙነት ሃላፊ አቶ ኤፍሬም ማዴቦ የተገኙ ሲሆን አቶ ኤፍሬም ስለ ወቅታዊው የድርጅታቸው ሁኔታና የነፃነት አርበኛውን አቶ አንዳርጋቸው ፅጌን በተመለከተ ሰፊ ንግግር ማድረጋቸውን ከስፍራው የተላከልን መረጃ ያመለክታል። በአሁኑ ሰአት በርካታአንዳርጋቸው ጽጌዎች ግንቦት 7 ትን እየተቀላቀሉ መሆናቸውን የገለፁት አቶ ኤፍሬም ነጻነታችንን በውጪ ሃይል መልካም ፈቃድሳይሆን በመስዋትነት በደማችን ዋጋ በመክፈል የሀገራችንንህልውና ከህወሃት ዘረኛ አገዛዝ ለመታደግ እልህ አስጨራሽየሆነው ትግል ላይ እንገኛለን በማለት፤ ለመላው የኢትዮጵያ ህዝብ ትግሉን ከዳር ሆነን የምንመለከትበት ጊዜ አክትሟልናሁላችንም የነፃነት ትግሉ አካል እንሁን ሲሉ ጥሪ አቅርበዋል።በስብሰባው ላይ ነዋሪነታቸው በኮሎራዶ ዴንቨርና አካባቢው የመጡበብዙ መቶዎች የሚቆጥሩ ኢትዮጵያውያን መሳተፋቸውን ለማወቅ ተችሏል።

በስብሰባው ላይ ንግግር ያደረጉ አንድ የሃይማኖት አባትየህወሃት ጉጅሌዎች ከነመሪዎቻቸው ሁሉም ፀይም ሞሶለኒ ናቸውበማለት ተሳታፊውን ያስደመመ ንግግር አድርገዋል። አክለውም ( ወደ ገጽ 4 ዞሯል )

## አዲስ አበባ ዉስጥ መለስን ለመዘከር በሚል ሰራተኞች ስራቸውን አቋርጠው ውይይቱን እንዲሳተፉ ታዘዙ

የዝክረ መለስ 2ኛ የሙት ዓመት አከባበርን ምክንያት በማድረግ በአዲስ አበባ በነበረው የፓናል ውይይት የመንግስትን ሰራተኛው ለግማሽ ቀን ስራ ሳይሰራ መዋሉን ዘጋያችን ገልጿል። በተለያዩ ቦታዎች የተዘጋጁትን የፓናል ውይይቶች የመስተዳድሩ የአመራር አባል አቶ ፋቃዱ ወ/አረጋይ፣ የአዲስ አበባ ሴቶችና ወጣቶች ቢሮ ኃላፊና የምክትል ቢሮ ኃላፊ በተናጠል መርተዋል። የወጣቶች መድረክ በሃገር ፍቅር አዳራሽ የሴቶች መድረክ በአዲስ አበባ ማዘጋጃ ቤት የባህል አዳራሽ እንዲሁም የልዩ ልዩ አካላት መድረክ በስድስት ኪሎ በሚገኘው የባህል ማዕከል የፓናል ውይይት ተካሂዷል።

በሶስቱም ውይይቶች ለተሳታፊዎች የሃሳብና የጥያቄ ማቅረቢያ ሰዓት በተጊቢው መንገድ ያላተሰጠ ሲሆን ሁሉም የመድረኩ ተናጋሪዎች አቶ መለስ ዜናዊን በማወደስ ላይ ትኩረት አድርገው ነበር። በመድረኩ ላይ አቶ መለስ ዜናዊ አዋቂመሪ፣ የሰብዓዊ መብት ታጋይ፤ የአፍሪካ መሪ፤ የመልካም አስተዳደር ችግርን የፈታ መሪ፤ የአለም መሪ፤ አለማቀፋዊ ደረጃ ያለው ጭንቅላት ባለቤት፣ ተዝቆ የማያልክ የእውቀትምንጭእንደነበር ተወስቷል። የመለስ ሌጋሲን ብቻ እየመነዘሩ መሄድ መሄድ እንደሚገባ የተነገረ ሲሆን መለስ በመሪነት ዘመኑ በተለያየ ጊዜ ያደረጋቸውን ቃለ መጠይቆች ( ወደ ገጽ 5 ዞሯል )

## “አሸባሪነት” በወያኔ አገዛዝ ሥር ባለችው ኢትዮጵያ

በአገራችን፣ በወያኔ አገዛዝ መደበኛ ትርጉማቸውን ከሳቱ በርካታ ቃላት መካከል “የሽብር ድርጊት“ እና ”አሸባሪ“ የሚሉት ግንባር ቀደሞቹ ናቸው። ሰፊ ተቀባይነት ያለው የአሸባሪ ትርጉም “የሽብር ድርጊቶችን የሚፈጽም ሰው ወይም ድርጅት” ማለት ነው። “የሽብር ድርጊቶች” የሚባሉት ደግሞ የተለመዱ ጥቃቶችን ሳይሆን የሀይማኖት፣ የፓለቲካ ወይም የርዕዮተዓለም ግብ ለማሳካት ሲባል በሰዎች ላይ ፍርሀትን ለማንገስ፤ በሰላማዊ ዜጎች ላይ የሚደርሱ አስከፊ ጥቃቶችን ነው። የሽብር ድርጊቶችን ሰላማዊውን ሕዝብ ጭዳ የሚያደርጉ በመሆኑ በጥብቅ ሊወገዙ ይገባል። ዓላማን በሽብር ድርጊቶች ማስፈፀም ተቀባይነት የሌለው ተግባር ነው።

በወያኔ መዝገበ ቃላት ግን “ሽብርተኛ” እና “የሽብር ድርጊቶች” በዘፈቀደ የሚነገሩ ተራ ቃላት ሆነዋል። ስለአገራቸው እና ስለትውልድ የሚጨነቁ፤ ሀሳባቸው በነፃነት የሚያራምዱ፤ የወያኔን ፕሮፖጋንዳ እንደ በቀቀን የማይደግሙ ዜጎች “አሸባሪዎች” እየተባሉ ወደ እስር ቤቶች እየተወረወሩ ነው። ጋዜጠኞች፣ ጦማርተኞች፣ ፍጹም ሰላምተኛ አማኞች እና ሰላማዊ ፓለቲከኞች በሽብርተኞች ዝርዝር ውስጥ ቀዳሚውን ሥፍራ የያዙ ናቸው።

በአንፃሩ ደግሞ እውነተኛው አሸባሪ ህወሓት፣ የመንግሥትን ሥልጣን ይዞ መላውን የኢትዮጵያ ሕዝብ ማሸበሩን በስፋት ተያይዞታል። ህወሓት ዘረኛ ርዕዮተ ዓለሙን ለማስፈፀም ሲል ባለፉት ሠላሳ አምስት ዓመታት ውስጥ የፈፀማቸው የሽብር ድርጊቶች ተዘርዝረው አያልቁም። የህወሓት የሽብር ድርጊቶች ዓላማ የኢትዮጵያን ሕዝብ በፍርሀት አደንዝዞ መግዛት ነው። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ደግሞ “አሸባሪ” የሚለውን ቃል ራሱ በማሸበሪያ መሣሪያነት እያዋለው ነው። ይህ የውስጥም የውጭም ታዛቢዎችን የሚያሳስት በመሆኑ ትኩረት የሚያሻው ጉዳይ ነው።

“የፀረ-ሽብር አዋጅ” የሚባለው ህገ-አልባነትን ህጋዊ ያደረገው ሰነድ የመንደር ካድሬዎች ሳይቀሩ አንድን ሰው በሽብርተኝነት “ጠርጥረው” ማሳሰርና ማስደብደብ አስችሏቸዋል። የአስተሳሰብ ድህነት ያጠቃቸው የህወሓት ካድሬዎች ብቻ ሳይሆኑ ኃላፊነት የጎደላቸው ፓሊሶችም የፀረ-ሽብር ህጉን ጉልበታቸውን ማሳያ እና ተፎካካሪዎቻቸውን ማጥቂያ አድርገውታል። በፀረ-ሽብር ህጉ ተከስሰው ወህኒ የወረዱ ዜጎችን ያጤነ ማንኛውም ሰው ኢትዮጵያ አገራችን በዚህ ህግ ሰበብ ምርጥ ዜጎቿን እያጣች እንደሆነ ይገነዘባል።

በሽብርተኝነት ለመጠርጠር የሚያበቁ ምክንያቶች እጅግ አሳዛኝ ናቸው። ለካድሬ ሰበካ እውነተኛነት ጥርጣሬውን የገለፀ አስተዋይ ሰው መሆን ብቻውን እንኳን በሽብርተነት ያስጠረጥራል። በዚህም ምክንያት ነው በእውቀትም በአስተሳሰብም የበሰሉ ዜጎቻን በአሸባሪነት የመፈረጅ እድላቸው ከፍተኛ የሆነው። የንቅናቄዓችን ዋና ፀሐፊ አቶ አንዳርጋቸው ጽጌን ጨምሮ በርካታ የሀገራችን ምርጥ ዜጎች የዚህ የተዛነፈ ትርጓሜ ሰለባ ሆነዋል። ተስፋ የሚጣልባቸው በርካታ ወጣቶች በዚህ ህገ-ወጥ ህግ እና የተሳሳተ ትርጓሜ ምክንያት የወጣትነት እድሜዓቸውን በእስር ቤት እንዲያሳፉ ተገደዋል። ከዚያ የበዙት ደግሞ በቃሉ ተሸማቀው፤ በሚያስከፍለው ዋጋ ተሸብረው ራሳቸውን እንዲደብቁ ተደርገዋል።

ለመሆኑ ኢትዮጵያ ያፈራቻቸው ምርጥ ዜጓቿ በአሸባሪነት ስም ወህኒ እየተወረወሩ ሲሰቃዩ ምላሻችን ምን ሊሆን ይገባል? እስከመቼ አስተዋይ፣ አርቆ አሳቢና አመዛዛኝ የሆኑ መሪዎቻችንን ለወያኔ ፋሽቶች እየገበርን እንኖራለን? ሀገራችን ይህን ኪሳራ የመሸከም አቅም አላት?

ግንቦት 7: የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ ወያኔን ለማስወገድ የተሻለ ነው ብሎ ያመነበት የትግል ስልት - ሁለገብ የትግል ስልት ነው። በዚህ የትግል ስልት መሠረት ሕዝባዊ ተቃውሞ፣ ሕዝባዊ እምቢተኝነት እና ሕዝባዊ አመጽ ተደጋግፈውና ተናበው መሄድ አለባቸው ብሎ ያምናል። ስለሆነም እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ በአመቸውና በሚያምንበት መንገድ ለትግሉ አስተዋጽኦ የማበርከት እድል አለው።

በዚህም መሠረት ለሀገር፣ ለትውልድ ድህንነት ዋጋ ለመክፈል እና ለገዛ ራሳችን ህሊና ታማኝ ለመሆን በወያኔ “አሸባሪ” ለመባል መድፈር የትግላችን አንዱ አካል አድርገን መቁጠር ይኖርብናል። በወያኔ “አሸባሪ” መባል የሚያሸማቅቅ ሳይሆን የሚያኮራ፤ ለታላቅ ኃላፊነት እና ሕዝባዊ አደራ በእጩነት የሚያቀርብ መሆኑን በራሳችንም በማኅበረሰባችንም ውስጥ ማስረጽ ይኖርብናል። “አሸባሪ” የሚለው ቃል በወያኔ ተግባር መሠረት ሲተረጎም “ለሀገርና ለትውልድ ደህነት የሚጨነቅ ምርጥ ዜጋ“ ማለት እንደሆነ ማስተማር ይገባናል።

ወያኔ ወደ ሕዝብ የሚወረውረውን ጦር መልሰን ወደ ራሱ መወርወር ይኖርብናል። ወያኔ አሸባሪነት ዜጎችን ለማጥቂያ እያዋለው መሆኑ ተረድተን እኛ በዚህ ስያሜ መሸማቀቅ ሳይሆን፣ መኩራትና መልሰን ወያኔን ማሸማቀቅ ይኖርብናል። በውጭ አገራት እየተስፋፋ የመጣው የወያኔ ሹማምንትን የማሸማቀቅ ዘመቻ በኢትዮጵያ ውስጥም መጀመር ይኖርበታል።

ሕዝባዊ ተቃውሞ፣ ሕዝባዊ እምቢተኝነትና ሕዝባዊ አመጽ ሲቀናጁ ድላችንን ያፈጥናሉ። በወያኔ “አሸባሪ” መባል የመልካም ዜግነት ምስክርነት እንደሆነ በሙሉ ልባችን እንቀበል።

**ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ!!!**

---

## በተለያዩ አሜሪካ ግዛቶች የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን

. . . ( ከገጽ 1 የዞረ )

ባለመሳካቱ፤ ደም የተከፈለበትን የአገሪቱን መሬት በበቆሎ ዋጋ እየቆረሰና እየሸነሸነ ለባዕዳን መቸርቸር ከጀመረ ሰነባብቷል በማለት ወያኔ ከጎንደርና ከጋምቤላ ሰፋፊ መሬቶችን ” የሱዳንግዛት ነው” በሚል ቁርሶ በመስጠቱ ሣቢያ፤ “የአገሬን መሬትአላስነካም” ያሉ ኢትዮጵያዊያን ቦታውን ላለመልቀቅ ባደረገው ትግል በርካቶች በግፍ በአገዛዙ ቅጥረኞች በጥይት ተደብድበው መገደላቸውን አስታውሰዋል።

ፋሽስቱ ወያኔ የኢትዮጵያን መሬት እየቆረሰ ለባዕዳን ሲያድልዝምታችን ምን የሚሉት ነው? ሲሉ የጠየቁት ኢትዮጵያውያኑ “ባለቤቱን ካልናቁ አጥሩን አይነቀንቁ” እንዲሉ፤ ወያኔ ይህንድርጊት በማናለብኝነት እየፈጸመ ያለውም የኢትዮጵያን ህዝብ በመናቁ እንደሆነም ጠቁመዋል። አስተያየት ሰጭዎቹ አያይዘውም፡-“ዘረኛው የህወሃት አገዛዝ ዝምታችንን ከፍርሃት ስለቆጠረውም፤ ከአያት ከቅድመ አያት የወረስነውን ይዞታችንን ሳይቀር ሊቀማን የእያንዳንዳችንን በር እያንኳኳ ነው በማለት ሁሉም ኢትዮጵያዊ በጋራ አገሩንና ርስቱን ከባንዳ አገር ሻጭ ወንበዴዎች እጅ ለመንጠቅ መታገል ያለበት አሁን ነው ሲሉ ጥሪ አቅርበዋል። በኢትዮጵያ ያለው የኑሮ ውድነቱና የህዝቡ ድህነት መላካልተበጀለት፤ የአገዛዙ ፅንፈኛ ዘረኝነት፤ ሙስና፤ ጭቆናና በደል በቃ ብለን መታገል ካልቻልን አገሪቱ ወደ አስፈሪ የመበታተን አደጋ ሊያጋጥማት እንደሚችል ኢትዮጵያውያኑ ስጋታቸውን አስቀምጠዋል። ፋሽስቱ ወያኔ የአገዛዝ ዘመኑንለማራዘም ሲል የአገሪቱን ህልውና እየናደ መሆኑን ልብ ልንልያሉት አስተያየት ሰጭዎቹ ኢትዮጵያን ከመበታተን ለመታደግና በእኩልነት ላይ የተመሠረተ አንድነቷን ጠብቆ ለማቆየት መነሳትየሚገባን አሁን መሆኑን ተገንዝበን በፅናት ልንታገል ይገባልሲሉ የአሁኑኑ እንነሳ የትግል ጥሪ ማቅረባቸውን ዘጋቢዎቻችን ከተለያዩ ግዛቶች ያጠናከሩት መረጃ ያመለክታል።

## የመከላከያ ሰራዊት አባላት ወያኔን ዘረኛ ስርዐቱን

. . . ( ከገጽ 1 የዞረ )

እዞች መተማመን ጠፍቶ ውጥረት መንገሱ ታውቋል። በእያንዳንዱ እዝ በመሪነትና በተቆጣጣሪነት የተመደቡ የአገዛዙ ቅጥረኞች ሳይቀር በተስፋ መቁረጥ ሞራላቸው በመውደቁ የሰራዊት አባላትን መቆጣጠር ባለመቻላቸው የሰራዊቱን መክዳት አባብሶታልሲሉም የደረሰን መረጃ ያሳያል። ይህ በእንዲህ እንዳለ በተለያዩጊዜያት እየተንከባለለ የመጣው የሰራዊቱ አቤቱታ እጅግ አደገኛአዝማሚያ እያሳየ በመምጣቱ፤ ዘረኝነትን መሰረት በማድረግ የተዋቀረው የሰራዊቱ አደረጃጀት ላይ ሰራዊቱ ማጉረምረም መጀመሩና፤ የሚከዳው ሰራዊት ቁጥር ከዕለት ዕለት እየናረ በመምጣቱ ከፍተኛ የሕወሓት ጄኔራሎች በየቀኑ ካለማቋረጥምስጢራዊ ስብሰባዎችን እያደረጉ መሆኑን ምንጮቹ ገልፀዋል።

በተያያዘ ዜና በተለያዩ እዞች የሚገኙ የመከላከያ ሰራዊትአባላት ለአባይ ግድብ ማሰሪያ፣ ለመለስ ፋውንዴሽንና ለሌሎችምከአገዛዙ የሚወርዱ የመዋጮ ትእዛዞችን አንከፍል በማለት በመቃወማቸው ሰራዊቱ ከአገዛዙ የጦር ጄኔራሎች ግጭት ውስጥ መግባቱና ግጭቱ አሁንም ድረስ አለመብረዱን ለማወቅ ተችሏል። በፋሽስቱ ወያኔ ወታደራዊ አዛዦችና በተራው ሰራዊት መካከልከፍተኛ የሆነ የኑሮ ልዩነት መኖሩንና አብዛኞቹ የመከላከያመኮንኖች የህወሃት አባላት ሲሆኑ፣ በአዲስ አበባ እናበኢትዮጵያ ዋና ዋና ከተሞች ዘመናዊ ቪላዎችንና ፎቆችን ሰርተውበወር በመቶ ሺዎች የሚቆጠር የኪራይ ገቢ እያጋበሱ እንደሚገኙ መዘገባችን ይታወሳል።

# እንደገና ይድረስ ለሠራቱ

"የትግሬ" ነፃ አውጪ ነኝ ብሎ ራሱን የሠየመው የዘረኞችና የዘራፊዎች ቡድን አገሪቷን እያንሳቆለ ያለው ከሠራዊቱ ጀርባ ተንጠላጥሎ መሆኑ ይታወቃል። ይህ የዘረኞችና የዘራፊዎች ቡድን የተሸከመውን ሠራዊት ሳይቀር በጉስቁልናና በድንቁርና እንዲኖር ፈርዶበታል። ህወሃት ሠራዊቱ እንዲማር፤ ዘመኑ ከሚፈቅደው የቴክኖሎጂ እውቀት ጋር ራሱን እንዲያዋህድ እና በራሱ የሚተማመን የዘመነ ሠራዊት እንዲሆን ፍላጎት የለውም።አሜሪካን በአገሯ በሚገኙ የጦር ትምህርት ተቋማት ውስጥ ወታደሮችን ለማሰልጠን ፍላጎት ብታሳይም ሳሞራ የኑስና መለስ ዜናዊ እምቢ ማለታቸውን አብዛኛው የሠራዊቱ አባላት የሰሙት አይመስልም። አሜሪካን በሁለት ዓመት ውስጥ ብቻ 42 ወታደሮችን አገሯ ወስዳ ለማሰለጠን በጠየቀች ግዜ ሳሞራ የፈቀደው 13 ወታደሮች ብቻ ሂደው እንዲማሩ ነው። እነዚህም ከህወሃቶች መካከል ፊደል የቆጠሩ ተፈልገው በመገኘታቸው መሆኑም ታውቋል። በሠራዊቱ ውስጥ የሚገኙ ሌሎች የትምህርት ዝግጅት ቢኖራቸውም የትምህርት እድሉን ተከልክለዋል።

ህወሃት ከራሱ ውጪ ያሉት ሌሎች ላይ ምንም ዕምነት እንደሌለው በተለያየ አጋጣሚ ተናግሮታል። የትምህርት ዕድሉን ለምን መጠቀም እንዳልፈለጉ ሲጠየቅ ሳሞራ የኑስ "ሌሎችን አናምናቸውም አሜሪካን ሂደው ይቀራሉ" ብሎ መልስ መስጠቱም ተመዝግቦ ይገኛል። 11ኛ ክፍልን ያልዘለለው የህወሃቱ ኢታማዦር ሹም ሳሞራ የኑስ ሠራዊቱን ታማኝና የማይታመኑ በሚል ይከፍላቸዋል። የህወሃት አባል የሆነ ወታደር ታማኝ ፤ ሌሎች የሠራዊቱ አባላት የማይታመኑ።

አሁንም የሠራዊቱ አባላት ስሙ !

እናንተ ምንም ያክል ጥሩ ዜጋ ለመሆን ብትጥሩ በህወሃቶች ዘንድ የምትታመኑ አይደላችሁም። ህወሃቶች ከእነርሱ ውጪ ባሉ ሌሎች ላይ ጥርሳቸውን እንደነከሱ እስከ ዛሬ አሉ። በሌሎች ዜጎች ላይ የመዘዙት የበቀል ሰይፍም ወደ ሰገባው የሚመለስ አልሆነም። በሁለት ዓመት ውስጥ 42 ወታደሮችን አሜሪካን ወደ አገሯ ወስዳ ለማሰልጠን ብትጠይቅም 13ቱን ብቻ ተቀብለው 29ኙን አንፈልግም ማለታቸው የተመዘዘው የበቀል ሰይፋቸው አንዱ አንጓ መሆኑን የትምህርት ዕድሉን የተነፈገው የሠራዊቱ አባል ልብ ሊለው ይገባል። እነ ሳሞራ የኑስ ከእነርሱ ውጪ ያሉ ሌሎች ዜጎች በድንቁርናና በችጋር እየተሰቃዩ ይኖሩ ዘንድ ፈርደውበታል። በእንዲህ ሁኔታ እንዲኖር የተፈረደበት ሠራዊት፤ ውጪ አገር ሂዶ እንዳይማር የተከለከለ ሠራዊት፤ ዘር ሃረጉ እና ድርጅታዊ ታማኝነቱ እየታየ ለሹመት የሚበቃው የሠራዊት አባል ይህን ውስኔ ለወሰነበት ለመለስ ዜናዊ ፋውንዴሽን ከሚያገኛት ከወር ደመወዙ ላይ ቆርጦ እንዲከፍል ይደረጋል። እንዲህ ዓይነት በደል በየትኛውም አገር ታይቶ አይታወቅም።

በችጋር እንድትኖሩ ከምታገኟት ከወር ደመወዛችሁ ላይ ይወሰዳል፤ ተምራችሁ ራሳችሁን እንዳትቀይሩ በነፃ የሚገኘውን የትምህርት ዕድል እንኳ እንዳትጠቀሙ ተከልክላችኋል። በዚህ ሁኔታ እንድትኖሩ ከተፈረደባችሁ በኋላ የገዛ ወገኖቻችሁን ደም በከንቱ እንድታፈሱ ትደረጋላችሁ። የቀደመው ትውልድ በደሙ ያቆመው ድንበር ፈርሶ እና ዜጎች ተፈናቅለው መሬቱ ለባዕድ ሲሰጥ አናንተ ቁማችሁ ትመለከታላችሁ። ያ የሚፈሰው ደም የራሳችሁ ደም፤ ተፈናቅሎ ሜዳ ላይ የሚወድቀው የገዛ ወገናችሁ መሆኑን ለማሰብ እንኳ ነፃነት ያጣችሁ ትመስላላችሁ። የህፃን ደም በአዲስ አበባ ጎዳና ላይ ሲፈስ ለምን ስትሉ አልተሰማም፤ ጋምቤላዎች ለዘለዓለም ከኖሩበት መሬት ተፈናቅለው መሬታቸውን ሌሎች ሲቀራመቱት ይሄ አይሆንም ለማለት የያዛችሁት ነፍጥ የሸንበቆ ምርኩዝ ሁኖባችኋል። በኦጋዴን ላይ የዘር ማጥፋት ወንጀል ሲፈፀም ተባባሪ ትሆናላችሁ። ህወሃቶች በዚያች አገር ለሚፈፅሙት ማንኛውም ወንጀል እናንተ የእነርሱ በትር ሁናችሁ ታገለግላላችሁ። ከዚያች አገር ከሚገኘው ሃብት ግን ተካፋይ አትሆኑም። እነርሱ ሚሊየነር ሁነው የሚያደርጉትን ሲያጡ፤ አናንተ የሠራዊቱ አባላት ግን በችጋር ከነ-ቤተሰቦቻችሁ ትሰቃያላችሁ። ይሄ ሁኔታ ማብቃት የኖርበታል።
የአገሪቷ መከላከያ ኃይል ራዕይ ተብሎ የተነገረህ እንዲህ ይላል *". . . ለህገ-መንግስቱ እና ለህዝቡ ፍፁም ታማኝ የሆነ . . . የሃገራችን ህዝቦች ተምሳሊት የሆነ . . . የእውቀት መፍለቂያ የሆነ ሠራዊት መገንባት "*

ምንም እንኳ ጥሩ ራዕይ ተቀርፆ የተቀመጠ ቢሆንም አንተ የሠራዊቱ አባል ግን የዚህ ራዕይ ተካፋይ አይደለህም።አንተ የምትካፈልው መከራውን እንጂ መልካሙን ራዕይ አይደለም። ለህገ-መንግስቱ እና ለህዝቡ ፍፁም ታማኝ የሆነ ሠራዊት መገንባት የሚለውን ራዕይ መልሰህ መልሰህ እንድታስብ እንመክርሃለን። በእኛ በኩል ግን ህወሃት በአገሪቷ ጫንቃ ላይ ከተቆናጠጠ ዘመን ጀምሮ ህዝቡን ሲያዋርድ ኖረ እንጂ ለህዝብ ታማኝ ሲሆን አልታየም። ህገ-መንግስት ብሎ ራሱ እዚያ ጫካ ሁኖ የፃፈውን ራሱ ሲያፈርሰው ኖረ እንጂ ሲያከብረው አላየንም። ህወሃት ለህገ-ማንግስቱ እና ለህዝቡ ታማኝ ሁኖም አያውቅም። ወደ ፊትም ራሱን ከህዝብ እና ከህግ-በታች አድርጎ እንዳይኖር እስከ ዛሬ ሲፈፅመው የኖረው ወንጀል የሚያስችለው አይሆንም። ህወሃቶች ከነ እድፋቸው ወደ ማይቀረው መቃብራቸው መሄድን የመረጡ ስለሆነ ሠራዊቱ ራሱን ከእነዚህ ነውረኞች ለይቶ ለህገ-መንግስቱና ለህዝቡ ፍፁም ታማኝ መሆኑን ማስመስከር ይጠበቅበታል።

ሌላው ከህወሃት ውጪ ያላችሁ የሠራዊቱ አባላት ልታስቡበት የሚገባው ዓቢይ ነገር ደግሞ 'የሃገራችን ህዝቦች ተምሳሊት የሆነ ሠራዊት መገንባት ' የሚለውን ራዕይ ነው። ሃገራችን ከ80 በላይ ብሄሮች የሚኖሩባት መሆኑ ይታወቃል።ለዚህች አገር ምሳሌ ሊሆን የሚችል መከላከያ ኃይል መገንባት እንደ ራዕይ የተቀመጠ ቢሆንም በተግባር የሆነው ግን ሌላ ነው። አሁን ባለው የአገሪቷ መከላከያ ኃይል ውስጥ ያሉ የጦር አዛዦችን ቀና ብለህ አይተህ እውነት መከላከያ ሃይሉ የህዝቦቿ ተምሳሊት የሆነ ሠራዊት መሆኑን ራስህ እንድትመልስ እንጠይቅሃለን። በአገሪቷ የተሾሙ ጄኔራሎች ከአንድ ጎጥ እና መንደር የተሰባሰቡ መሆናቸው በምን መልኩ የሃገራችን ህዝቦች ተምሳሊት የሆነ ሠራዊት ሊሆን እንደሚችል ህወሃቶችን ደግሞ ደጋግሞ መጠየቅ ተገቢ ይሆናል።

በመጨረሻም 'የዕውቀት ምንጭ የሆነ ሠራዊት መገንባት' የሚል ራዕይም በጉልህ ተፅፎ ተቀምጧል። የህወሃት የጦር አበጋዞች ከ7ኛ ክፍል ያልዘለሉ፤ካርታ ይዘው የቆሙበትን ሥፍራ እንኳ ለማሳየት የሚደናበሩ መሆናቸው የታወቀ ነው። እነዚህ ፊደል ቆጥረው ያልዘለቁ ቡድኖች የሚመሩት ተቋም እንደምን ሁኖ የዕውቀት ምንጭ ሊሆን እንደሚችል የሚያውቅ የለም። የህወሃቶች እውቀት የንፁሃን ደም ማፍሰስ፤ የድሃ ሃብት መዝረፍ፤ እኔ ብቻ ባይነት እንጂ ከዝህ የዘለለ ሌላ እውቀት ያላቸው አይደሉም። እነርሱ ባለመማራቸው የጎደለባቸው ነገር አለመኖሩን እያዩት ለትምህርትና ለተለየ ዕውቀት ዋጋ ይሰጣሉ ማለት አይቻልም። ሌሎቹም ተምረው እውቀት እንዲገበዩ ለማድረግ ስብዕናቸው አይፈቅድላቸውም። በዚህም ምክንያት ከውጭ አገራት በነፃ የሚገኘውን የትምህርት ዕድል እንኳ ወታደሩ ተጠቅሞ ራሱን በእውቀት እንዳያዳብር ይከለክላሉ። እንዳይማር የተከለከል የሠራዊት አባል እንደምን ሁኖ የዕውቀት መፍለቂያ ሊሆን እንደሚችል የሠራዊቱ አባላት የሽፍቶቹን ቡድኖች መጠየቅ ይኖርባችኋል።

የሠራዊቱ አባል የህዝብ አካል መሆንህን አትርሳው። ነገ ዞረህ የምትገባውም እዚያው ከወጣህበት ህዝብ መሆኑን እኛ ልናስታውስህ እንወዳለን። አሁን ባለው አካሄድህ የወጣህበትህን ድንኳን፤ በዚያች ድንኳን ውስጥ ሁነህ ያሳደጉህ ወገኖችህን እያሳደድክ መሆንህን አስታውስ። የወጣህበትንም ድንኳን እያፈረስክ ነው። ድንኳንህንም አፍርሰህ ከጨረስከው ነገ ዞሮ ማረፊያ እንደማይኖርህ ደግሞ እኛ ልናስታውሰህ እንፈልጋለን። ጥሪያችንን መስማት ከማንም በላይ ለራስህ ይበጅሃል።የወገኖችህን ጥሪ ሰምተህ በወገኖችህ ላይ የተመዘዘውን የበቀል ሰይፍ ለማቆም ከህዝብ ጎን መሆንን አልመርጥ ካልክ መጨረሻህ አያምርም።እነ ሳሞራ የኑስ ጠላቶችህ እንጂ ወገኖችህ አይደሉም። እነ ሳሞራ የኑስ አንተንና ልጅ ልጆችህን ጭምር በድንቁርና አዘቅት ውስጥ አኑረው ቀጥቅጠው ለመግዛት ያላቸው ፍላጎት ወሰን እንደሌለው ማወቅ ይኖርብሃል። የተሸከምከው መሣሪያ ለፍትህ፤ለእኩልነት፤ ለነፃነት እና ለእውነተኛ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ እንቅፋት የሚሆኑትን የሚፋለም ሊሆን ይገባዋል እንጂ እነዚህን ጥያቄዎች ባነሱ ወገኖች ላይ የሚያነጣጥር መሆን አይኖርበትም።

እንግዲህ ምን እናድርግ እያላችሁ የምትጠይቁን አላችሁ። ለዚህ ጥያቄ መልሱ ያለው ከእናተው ደጅ ነው። እኛ ያነሳነውን ጥያቄ ባላችሁበት ሁናችሁ ማንሳት ትችላላችሁ። አብዛኛው ሠራዊት ጥቂት ዘረኞችንና ዘራፊዎችን ተሸክሞ የሚኖሩበት ሁኔታ ለመቀየር ሦስትም አራትም እየሆናችሁ እምቢ ማለት መጀመር አለባችሁ። ህወሃቶችን ተሸክማችሁ፤ የህዝባችሁ ጠላቶች ሁናችሁ፤ አገራችሁንና ህዝባችሁን አዋርዳችሁ የምትኖሩት ኑሮ ኑሮ አይደለምና እምቢ አይሆንም ማለት ጀምሩ። ለዘረኞቹና ለዘራፊዎቹ ህወሃቶች ከመሞት ይልቅ ለፍትህ፤ለእኩልነት እና ለነፃነት ብላችሁ ብትሠው መሥዋእትነታችሁ ለዘላለም ሲዘከር ይኖራል ፤ስማችሁም ከመቃብር በላይ ይሆናል።ፍፃሜያችሁም የጀግና ፍፃሜ ይሆናል።

ፍፃሜያችሁ የጀግና ፍፃሜ እንዲሆን ለፍትህ፤ ለነፃነት እና ለእኩልነት ዘብ የምትቆሙ ሁኑ እንጂ የአንድን ዘረኛና ዘራፊ ቡድን እድሜ ለማራዘም የምትቆሙ አትሁኑ።

**ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ!!!**

..........................................................................................................

## ወያኔ በ40 በ60 ዕቅድ የሚሰሩ ቤቶች ከመጪዉ ምርጫ በፊት ተጠናቅቀዉ ለባለገንዞቦች እንዲሰጡ አዘዘ

በወያኔ ቋንቋ 40 በ60 በሚባለው የቤቶች መርሃግብር የታቀፉ የዲያስፖራ አባላት ከቀጣዩ ዓመት ምርጫ በፊት ይሰራላችኋል የተባለዉ ቤት ግንባታዉ ተጠናቅቆ እንዲሰጣቸው የአዲስ አበባ መስተዳድር መመሪያ መስጠቱ ታወቀ። ወያኔ ቤትና መሬት እሰጣችኋለሁ እያለ በቢሊዮኞች የሚቆጠር ገንዘብ የሰበሰበዉ በአብዛኛዉ እዚያዉ አጠገቡ ከሚኖረዉና በሙሉ ድምጽ መርጦኛል ብሎ ከሚናገረዉ ግብር ከፋይ ህዝብ ቢሆንም ዛሬ የተወሰኑ ሰዎችን ለማስደሰት ጥድፊያዉን የያዘዉ ግን በጥቅም ደጋፊዎቹ የሆኑትን አንዳንድ የዳያስፖራ ሆዳሞች ለማስደሰት ነዉ።

ወያኔ ቤት ሰርቼ እሰጣቸኋለሁ ብሎ ቃል ገብቶ ገንዘብ የተረከባቸዉን ሰዎች የቤት ፍላጎት ለማርካት በትንሹ ከ16 ዓመታት በላይ ጊዜን እንደሚወስድ የደረሰን መረጃ ያመለከታል። የአዲስ አበባ ቁጠባ ቤቶች ኢንተርፕራይዝ እስካሁን 13ሺህ 800 ቤቶችን በሰንጋተራና ቃሊቲ ክራውን ሆቴል በመሳሰሉ አካባቢዎች ላይ እየገነባ መሆኑ የሚታወቅ ሲሆን፣ እነዚህን ቤቶች እስከሚቀጥለው ዓመት አጋማሽ ድረስ ለዕድለኞች ለማስተላለፍ ታቅዷል የአስተዳደሩ ምንጮች እንደገለጹት ቤቶቹ ከቀጣይ ዓመት ምርጫ በፊት ሙሉበሙሉ ተጠናቀው እንዲተላለፉ ከአስተዳደሩ መመሪያ ተሰጥቷል። ሆኖም ለምሳሌ ለ40 በ60 የቤቶች ፕሮግራም የተመዘገበው ጠቅላላ ሕዝብ ቁጥር 164 ሺህ 779 ያህል ሲሆን የወያኔ አገዛዝ  ግን በዓመት ከ10 ሺህ ቤቶች በላይ የመገንባት አቅም ባለመፍጠሩ የተመዘገቡትን ብቻ ለማዳረስከ በጣም ብዙ ዓመት እንደሚፈልግ የአስተዳደሩ ምንጮች አስታውቀዋል። ይህደግሞ ከዛሬ ነገ የመኖሪያ ቤት ባለቤት እሆናለሁ ብሎ ተስፋ ላደረገው ሕዝብ ተስፋ አስቆራጭ ዜና ነው ብለዋል።

በ20/80 በተለምዶ ኮንዶሚኒየም ፕሮግራም የምርጫ 97ን መቃረብ ታሳቢ አድርጎ ሲጀመር  ከ350ሺ በላይ የአዲስ አበባነዋሪ መኖሪያ ቤት እፈልጋለሁ ብሎ መመዝገቡን ያስታወሱት ምንጮቹ፣ ፕሮግራሙ 10 ዓመታት ያህል ቆይቶ መመለስ የቻለው ግን 100 ሺ በታች ቤት ፈላጊዎችን ጥያቄ ነው ብለዋል። በዚህ መረጃ መሠረት የጠቅላላ ተመዝጋቢውን ፍላጎት ለሟሟላት ተጨማሪ ከ20 ዓመታት በላይ ጊዜን እንደሚወስድ አፈጻጸሙ በራሱ የሚናገር ነው ሲሉ አስረድተዋል።

## ወያኔ በዉጭ አገሮች የገጠመዉን ከፍተኛ ዉርደትና ተቃዉሞ አስመልክቶ በየአገሩ የሚገኙ አምባሳደሮቹን ጠራ

ዘረኛዉ የወያኔ አገዛዝ በቅርቡ አሜሪካ መጥቶ የስራ ጉብኝት ያደረገዉ ከፍተኛ የልዐካን ቡድኑ የደረሰበትን ዉርደት በተመለከተና ከዳያስፖራዉ አገኛለሁ ብሎ በዕቅድ የያዘዉ የዉጭ ምንዛሬ ካገኘዉ ጋር ሲተያይ እጅግ በጣም ዝቅተኛ በመሆኑ በአለም ዙሪያ የሚገኙ 46 አምባሳደሮችና ቆንስላ ጽሕፈት ቤቶች ሀላፊዎችን አዲስ አበባ ጠርቶ ግምገማ መቀመጡ ተሰማ። አምባሳደሮችና ዲፕሎማቶች ለአምስት ቀናት ውይይት የሚያካሂዱ ሲሆን፣ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ ዶ/ር ቴድሮስ አድሃኖም ኢኮኖሚክ ዲፕሎማሲው የተሳካ እንደነበር ሲናገር ተደምጧል። ዶ/ር ቴድሮስ ከዚህ በተጨማሪ ብዙ መሻሻል ያለባቸው ሥራዎች መኖራቸውን ገልጾ፣ ትላልቅ ኩባንያዎች ኢትዮጵያ ውስጥ መዋዕለ ንዋያቸዉን እንዲያፈስሱ ለማድረግ የዉጭ ባለሀብቶች እንዲያደርጉ ያለባቸውን ችግር እየለዩ ድጋፍ ማድረግ እንደሚገባ አሳስቧል።

ሚኒስትሩ ኢንቨስተሮች ሁሉ አንድ ዓይነት ችግር እንደሌለባቸው ጠቁመው፣ «የመሬት ችግር ያለባቸው ሁለት ኢንቨስተሮች ቢኖሩ፣ አንደኛው መሬት ተሰጥቶት ግን ደግሞ ነዋሪዎች ካሳ ተሰጥቷቸው ባለመነሳታቸው የተስተጓጐለበት ይሆናል። በሌላ በኩል ጭራሹኑ መሬት ያልተሰጠው ሊሆን ስለሚችል ለያይቶ ማየት ያስፈልጋል፤» በማለት ይህንን ጉዳይ ከዲፕሎማቲክ ማኅበረሰቡ ውጪ ያሉ የመንግሥት ተቋማት በዚህ መንገድ ሊሠሩ እንደሚገባ አስገንዝበዋል።

የወያኔዉ የዉጭ ጉዳይ ሚኒስቴር መሻሻል አለባቸው ካላቸው ጉዳዮች መካከል የዳያስፖራ ቤቶች ልማት፣ የቢጫ ካርድ አሰጣጥ፣ የቦንድ ሽያጭ፣ የፐብሊክ ዲፕሎማሲና የአገርህን እወቅ ፕሮግራሞች ዋና ዋናዎቹ ሲሆኑ፤ በእነዚህ አካባቢዎች ማንናታቸዉንና አገራቸዉን በጥቅማጥቅም ከለወጡ  ጥቂት ግለሰቦች ዉጭ ዳያስፖራዉ በግልጽ ከወያኔ ጋር አንዳማይተባበር በተግባር አሳይቷል። በአዲስ አበባ ከተማ ከዓመት በፊት ይፋ የተደረጉት የቤት ልማት ፕሮግራሞች ለዳያስፖራ ጭምር የተዘጋጁ እንደነበሩ ተገልጾ ነበር። ነገር ግን ዳያስፖራው ከተለያዩ የአገሪቱ ክፍል የመጣ በመሆኑ በፈለገበት አካባቢ የቤት ባለቤት ሊሆን ይገባል የሚል የአቅጣጫ ለውጥ በመደረጉ፣ ክልሎች መመርያ እንዲያወጡ መግባባት ላይ ተደርሷል። ነገር ግን ሁሉም ክልሎች ወጥ በሆነ ደረጃ መመርያውን ባለማውጣታቸው የቤት ልማት ሒደቱ በሚፈለገው ፍጥነት መጓዝ አልቻለም። ስለዝህም  መመርያ ያወጡ ክልሎች ቀድመው ወደ ሥራ እንዲገቡ ውሳኔ መስጠቱንና አምባሳደሮቹም በዚሁ መሠረት ዳያስፖራውን ማስተናገድ እንዲጀምሩ የሥራ መመርያ ሰጥተዋ።

ቴዎድሮስ አድሃኖም የህዳሴዉን ግድብ ጨምሮ ኢትዮጵያ ውስጥ ለሚካሄዱ የልማት ሥራዎች በቦንድ ሽያጭ፣ ሀብት የማሰባሰብ ተግባር ሲካሄድ ቆይቷል ካለ በኋላ ፤ ሆኖም ብዙ ገንዘብ ይገኝበታል የተባለው የአሜሪካ ቦንድ ሽያጭ፣ በተለይ ባለፈው ዓመት አልተካሄደም ማለት ይቻላል ብሏል።  ሆኖም አሜሪካ ዉስጥ ቦንድ ሽያጭ ማካሄድ ያልተቻለዉ ዳያስፖራዉ ባደረገዉ ከፍተኛ ተቃዉሞ መሆኑ እየታወቀ ቴድሮስ አድሃኖም ግን ይህ የሆነበት ምክንያት የኢትዮጵያና የአሜሪካ ሕጎች የተለያዩ በመሆናቸው ነዉ ብሏል።  የሚገርመዉ ይህ የሚናገረዉን ነገር እንኳን በሚገባ አጣርቶ የማይናገር ሰዉ ሕጉን ለማስተካከል እየተሞከረ ነዉ ካለ በኋላ ከተባበሩት ዓረብ ኤምሬትስ በስተቀር የሁሉም አገሮች የቦንድ ሽያጭ ደካማ መሆኑን ተናግሯል።

## ቴዎድሮስ አድሃኖ "የድምፃችን ይሰማን" መሪዎችን .

. . ( ከገጽ 1 የዞረ )

ሴራ መሆኑን የሚናገሩት ጥቂቶች አለመሆናቸውን ለማወቅ ተችሏል። ቴዎድሮስ አድሃኖ ከአልሸባብ ጋር በተያያዘ ተይዘዋል የሚሏቸውን ተጠርጣሪዎች ከሙስሊሙ የመፍትሄ አፈላላጊ ኮሚቴ አባላት ጋር ለማገናኘት ሙከራ ማድረጉ ህዝበ ሙስሊሙን ማስቆጣቱም ታውቋል።

ድምፃችን ይሰማ ያወጣው መግለጫ እንደሚያመለክተው ቴዎድሮስ አድሃኖ ያነሳው የጓንታናሞ ግንኙነት ጉዳይ የመፍትሄ አፈላላጊ ኮሚቴ አባላትን የማይመለከት መሆኑን ድምፃችን ይሰማ አመልክቷል። የሙስሊሙ ማህበረሰብ ካለፉት 3 አመታት ጀምሮ በስላማዊ መንገድ የታሰሩ የመፍትሄ አፈላላጊ ኮሚቴ አባላት እንዲፈቱ ጥያቄ ማቅረባቸው የሚታስ ነው። የአሜሪካ አለማቀፍ የሃይማኖት ነፃነት ኮሚሽን እና ሌሎች አለማቀፍ የስብአዊ መብት ተሟጋች ድርጅቶች የጉጅሌው ወያኔ በቁጥጥር ስር ያዋላቸውን የሙስሊም መፍትሄ አፈላላጊ ኮሜቴ አባላት እንዲፈቱ በተደጋጋሚጥያቄ ሲያቀርቡ እንደነበር ይታወሳል።

## አሜሪካ  ዴንቨር "እኔም አንዳርጋቸው ጽጌ ነኝ" በሚል

. . . ( ከገጽ 1 የዞረ )

ህወሃት ማለት ሀጺያት ነው፣ ምክንያቱም ህወሃት ገዳይ ነው፤መግደል ደግሞ በመጽሃፍ ቅዱስ ሀጺያት መሆኑን እናውቃለንበማለት ከዚህ በኋላ እስከ ሂዎቴ ፍጻሜ ለሀገሬ፣ ለባንዲራዋ ክብር ለሚደረገው ትግል አጋርነቴንና ድጋፌን እሰጣለሁ ሲሉ ገልፀዋል። ሌላኛው ተናጋሪ አክቲቪስት አበበ ገላው እኔምይህንን የአንዳርጋቸው ጽጌን መልካም አርአያ አንግቤ ለሀገሬበየትኛውም መንገድ ላገለግል ቃሌን አድሻለሁ በማለት ግንቦት 7ትን የተቀላቀለበትን ሁኔታ በመግለጽ የተቀላቀሉን ጥሪም ለመላው የኢትዮጵያ ህዝብ አቅርቧል።

በስብሰባው ላይ ተሳታፊዎች አስተያየታቸውን ያለገደብ የገለፁበት ሁኔታም እንደነበር ለማወቅ ተችሏል። ከተሰነዘሩ አስተያየቶች መካከልም ተባብረን ፋሽስቱ ወያኔን የማስወገጃጊዜው ዛሬ ነው፤ በአቶ አንዳርጋቸው ጽጌ እየደረሰ ያለው ስቃይ ሊሰማንና ሊያባንነን ይገባል፤ የምንተኛበት ጊዜ አብቅቷል በጋራጠንክረን የመታገያ ጊዜው አሁን ነውና ሁሉም ኢትዮጵያዊ በዘር፤ በሃይማኖት ሳይንለያይ በጋራ እንነሳ የሚሉ ይገኙበታል።

በመጨረሻም የገንዘብ ድጋፍ ማሰባሰብያ የተደርጎ ፕሮግራሙ መፈፀሙን ለማወቅ ተችሏል። ይህ በእንዲህ እንዳለ ግንቦት 7 የፍትህ፤ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ ተመሳሳይ ህዝባዊ ውይይቶችንና የድጋፍ ማሰባሰብያ ፕሮግራሞች በተለያዩ የሰሜን አሜሪካ፤ አውሮፓና አውስትራልያ ግዛቶች ለማድረግ ከፍተኛ እንቅስቃሴ መጀመሩን የደረሰን መረጃ ያመለክታል።


**የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ  የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።**

<u>መካከኛ ሞገድ</u>:- በ 358 MB, በ 837 kHz
<u>አጭር ሞገድ</u>:- በ 31 MB  በ 9700 KHz
**በ 41 MB በ 7185, በ 7175 በ 7160 እና  በ 7120 KHz**
**በ 49 MB በ  5980 KHz እና  በ 60 MB  4760 GHz**

ላይ ዘወትር ማክሰኞ እና ሐሙስ ከጠዋቱ 2:30 እስከ 3:00 ሰዓት በድጋሜም ከሰዓት በኋላ 11:30 እስከ 12:00 ሰዓት እንዲሁም ዘወትር ቅዳሜ ከጠዋቱ 3:00 እስከ 3:30 ሰዓት እንዲሁም ከሰዓት በኋላ ከምሽቱ 11:30 እስከ 12:00 ሰዓት የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ **በስልክ** ወይም **በኢሜል** በንቅናቀያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን።

<u>ማሳሰቢያ</u>:- ሰዓቱ በኢትዮጵያ የሰዓት አቆጣጠር ነው።



**ውድ አንባቢዎቻችን**

ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታሰቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዎን ክፍላችን ወይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው  የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዛችንን እናቀርባለን። g7radio@ginbot7.org

## ወያኔ በግንቦት 7 ንቅናቄ ዙሪያ የተለመደ

. . . ( ከገጽ 1 የዞረ )

ለመፈረጅና ለመወንጀል የሃሰት ምስክርነት በሰልጣኝ የድራማው ተሳታፊ ግለሰቦች እንደሚሰጥም ተመልክቷል። የፋሽስቱ ወያኔ በብዙ ሚሊዮን ዶላር የሚቆጠር የአገር ሃብት በመመደብ በተደጋጋሚ ኢሳትን ከአየር ለማውረድ ከፍተኛ ሙከራ ማድረጉ የሚታስ ሲሆን ይህም ኢሳት ትክክለኛ መረጃ በማድረስ በኢትዮጵያ ህዝብ ዘንድ ሰፊ ድጋፍ አድማጭና ተመልካች በማትረፉእና በአገር ቤት ለሚንቀሳቀሱ የፖለቲካ ድርጅቶች ድምጽ በመሆን በማገልገሉ ላይ በመሆኑ አገዛዙ ኢሳትን የስልጣን ህልውናው አደጋ መሆኑን በመረዳቱ እንደሆነ በስፋት መነገሩን መዘገባችን ይታወሳል።

ክቡራንና ክቡራት አድማጮቻችን የፋሽስቱ ወያኔ አገዛዝ ዘመናዊ የማሰቃያ ዘዴዎችንም ጭምር በመጠቀም ከፍተኛ ሰቆቃ እየፈጸመባቸው በምድር ሲኦል ውስጥ የሚገኙትን አቶ አንዳርጋቸው ጽጌን በመጠቀም ለመልቀቅ በዝግጅት ላይ ስላለው ድራማ የውስጥ መረጃዎቻችንን አጠናክረን ሰፊ ዘገባ በቅርቡ እንደምናቀርብበዚህ አጋጣሚ ለማሳሰብ እንወዳለን።

## አዲስ አበባ ዉስጥ መለስን ለመዘከር በሚል ሰራተኞች

. . . ( ከገጽ 1 የዞረ )

ማንበብ እንደሚገባ ለሰራተኛው ተነግሯል። መለስ “ድህነትን ያስወገደ፤ የሃገርና የትውልድ ችግር የቀረፈ፤ የመልካም አስተዳደር ችግርን ገና ተማሪ እያለ ጀምሮ የሚያውቅ፤ የውጪ ጉዳይ ፖሊሲው በሰላምና በድህነት ላይ ብቻ እንዲመሰረት ያደረገ፤ የኢትዮጵያን ሉዓላዊነት ያስከበረ፤ በአፍሪካ መሪዎችና በዓለም መሪዎች ስብሰባ ላይ ተጽእኖ ሲፈጥር የነበረ፤ በእውቀትና በንባብ ላይ የተመሰረተ ትንታኔ የሚሰጥ፣ የህዳሴ ግድብን መሰረት የጣለታሪካዊመሪ” መሆኑን በማወቅ ፣ ማንኛውም ዜጋ የእሱን ሌጋሲ ማስቀጠል እንዳለበት በመድረኩ ላይ ተወስቷል።

የመለስ ሌጋሲ የአፍሪካም ሌጋሲ እንደሆነም ተገልጿል። በማዘጋጃ ቤት በነበረው የሴቶች መድረክ ከተሳታፊ ሴቶች ምንም ጥያቄ ሳይነሳ ውይይቱ ያለቀ ሲሆን ፣ መድረክ ላይ ስታወያይ የነበረችሁ የአዲስ አበባከ ተማሴቶች ወጣቶችና ህፃናት ቢሮ ኃላፊ በመድረኩ ላይ ማይክራፎኑን ተቀብላ ማልቀሷን ዘጋቢያችን ገልጻለች። በሀገር ፍቅር በነበረው መድረክ ደግሞ ስለመለስ ብዙ ገለጻዎች ከተሰጡ በኋላ፣ ተሳታፊው አስተያየት እንዲሰጥበት እድል ሲቀርብ፣ አንድ ተሳታፊ” ስለመለስ ብዙ ተብሏል፣ ነገር ግን በአዲስ አበባ ብዙ ቁጥር ያላቸው ዜጎች ዳቦ መብላት አልቻሉም።የኑሮ ውድነቱ ሰማይ ነክቷል። እናንተ ድህነት ጠፍቷል ትላላችሁ” እያለ መናገር ሲጀምር፣ መድረክ ላይ ያሉ ሰዎች አስቁመውታል።

ጠያቂው ያነሳውን ጥያቄ ለመደገፍና ንግግሩ እንዲቋረጥ መደረጉን ለመቃወም በሚመስል መልኩ አዳራሹ በጭብጫ የተናጋ ሲሆን፣ የመድረኩ መሪዎች ”እንዲህ አይነት ጥያቄዎች በሌላ የመልካም አስተዳደር መድረኮች የሚመለሱ በመሆናቸውና የዛሬው ውይይት በዝክረ መለስ ላይ ብቻ ማተኮር እንደለበት በማሳሰባቸው ከድጋፍ ማብራሪያ ውጪ ሌላ የተቃውሞ ሃሳብ ሳይነሳ መቅረቱን በውይይቱ የተሳተፈው ዘጋቢያችን ገልጿል።

አወያዩ አቶ ፋቃዱ ወ/ገብርኤል “አንድ በሽተኛ የሬዲዮ እና ቴሌቪዥ ጣቢያ አለ፣ኢትዮጵያን በመንግስታዊ ድርጅቶች እንድትጥለቀለቅ አድርጌ በእርዳታ ሃገሪቱን እመራታለሁ ብሎ የሚያስብ ብለው የተናገሩ ሲሆን፣ የጣቢያውን ስም ከመግለጽ ተቆጥበዋል። ንግግራቸውን በመቀጠልም “መንግስት ስለ ልማት ይለፈልፋል! ሙብራት ግን ይጠፋል፤ መንግስት ስለልማት ይለፈልፋል! ውሃ ግንይጠፋል፤ መንግስት ስለ ልማት ይለፈልፋል! ትራንስፖርት ግን ይጠፋል” በማለት ህዝቡ እንደሚናገር ገልጸው፣ ይህ አስተሳሰብ እንደማይጠቅም፣ የያዝነውን ልማት በአግባቡ ይዘን ለሌላው ጠንክረን መስራት ብቻ ነው የሚያዋጣን ብለዋል። በ3ቱም መድረኮች ተሳታፊ የነበሩት በአዲስ አበባ መስተዳድር ስር የሚገኙ ከወረዳና ክ/ከተማ በላይ ያሉ የሁሉም ቢሮዎችና ተቋማት ሰራተኞች ናቸው። ኢሳት ዝክረ መለስ በአል አከባበር ዝርዝር መመሪያው የደረሰው ሲሆን፣ ከመመሪያው ለመረዳት እንደሚቻለው መለስና ልማታዊ ዲሞክራሲያዊ መንግስት፣ መለስና የህዳሴው ግድብ፣ መለስና የድህነት ጥላቻ፣ መለስና ብህሃነትን በብቃት ማስተናገድ፣ መለስና የረቀቀ የዲፕሎማሲ ትግል በሚሉ ርእሶች ዙሪያ በመላው አገሪቱ ውይይቶች ይካሄዳሉ፡፤ ከዚህ በተጨማሪ መለስ በራሱ ንግግር በተመረጡ ጉዳዮች ላይ ያደረጋቸው ንግግሮች በሚዲያ እንዲቀርቡ እንዲደረግ በመመሪያው ላይ ተቀምጧል።

በሌላ ዜና ደግሞ በአዲስ አበባ ሚሊኒየም አዳራሽ በጠ/ሚ/ር ኃይለማርያም ደሳለኝ የሚመራ 2ኛው ሃገራዊ የመልካም አስተዳደር ውይይት እየተካሄደ ነው። የከፍተኛ ት/ት ተቋማት አመራሮች፤ የክልል መስተዳድሮች፣ የቢሮ ኃላፊዎችና ሚኒስትሮች ስብሰባ እያካሄዱ መሆኑ ታውቋል። አቶ አዲሱ ለገሰ ኢህአዴግ በገጠመው የአመራር ችግር የተነሳ የትራንስፎርሜሽንኑን እቅድ ለማሳካት አለመቻሉን መግለጻቸው ይታወቃል። ኢህአዴግ ከፍተኛ አመራሮች እያደረጉት በሚገኘው ስብሰባ የአመራር ችግሩ ዋናው የመመያያ አጀንዳ ይሆናል ተብሎ ይጠበቃል።